# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 2 ቁጥር 66 ህዳር 30 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## < <የኢዜማ ፖሊሲ እየተቀረጸ ያለው በባለሙያዎች እንጂ በፖለቲከኞች አይደለም፡፡> >

ይመስገን መሳፍንት



# ቆይታ

## < <የኢዜማ ፖሊሲ እየተቀረጸ ያለው በባለሙያዎች እንጂ በፖለቲከኞች አይደለም፡፡> >

ይመስገን መሳፍንት

የዚህ ሳምንት የዜጎች መድረክ የ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳችን የኢዜማ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ አባል ይመስገን መሳፍንት ናቸው፡፡ ይመስገን መሳፍንት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በሶሾዮሎጂ እና ሶሻል አንትሮፖሎጂ ያገኙ ሲሆን የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሶሻል ወርክ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተቀብለዋል፡፡ በዩኒቨርስቲ ኦፍ ሳውዝ አፍሪካ የሶስተኛ ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ የተለያዩ ተቋማትን በማማከር እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ኢዜማ አሰናድቶ ለውይይት ባቀረባቸውና እየቀረፃቸው በሚገኙ ፖሊሲዎች ዙሪያ ከይመስገን መሳፍንት ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ!



*ፖሊሲ ሲባል ምን ማለት ነው? ኢዜማስ ፖሊሲ ላይ አተኩሮ እንዲሰራ ያደረገው ዐብይ ጉዳይ ምንድን ነው?*

ፖሊሲ ማለት መንግሥት ለሚሰራቸው ሥራዎች የሚተገብራቸው ዝርዝር አላማና ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡ መንግሥት ለመሆን የተደራጀ ፓርቲ ሁሉ አማራጭ ሊኖሩት ይገባል፡፡ ኢዜማ ከተመሠረተ ጀምሮ በፖሊሲ ጉዳይ ሰፊ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል፡፡ በብሔራዊ አስፈጻሚ ውስጥ ጥናትና ምርምር ላይ የሚሰራ ኮሚቴ አለው፡፡ የምርጫ ዝግጅቱም ላይ በምርጫ ፖሊሲ ጉዳይ ላይ የሚያስተባብር ተወካይ አለው፡፡ ኢዜማም ፖሊሲ ላይ መሠረት ያደረገ ፓርቲ መሆኑ በሁሉም ይታወቃል፡፡

ኢዜማ ፖሊሲን ዐብይ ጉዳይ አድርጎ የተነሳው የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ፣ በሀሳብ ክርክሮች ለመቅረብ ነው፡፡ አላማችንና ዝርዝር የማስፈጸሚያ ስልታችንን በእያንዳንዱ ሴክተር ላይ አዘጋጅተናል፡፡ ጥልቅ የሆኑ የፖሊሲ ሃሳቦቻችንን የምናሳይበትን ቦታዎች ለይተናል፡፡ የሕብረተሳባችንን ችግር ከመፍታት አንጻር ከፖሊሲ አማራጭ ውጪ ሌላ የምንፈታበት ምንም መሳሪያ አይኖረንም፡፡ ኢዜማ በምሥረታው ወቅት ያጸደቀው የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚና የፖለቲካዊ ጉዳዮችን በፕሮግራሙ ላይ አሉ፡፡ ከእነሱ በመነሳት የፖሊሲ ጉዳዮችን በመቅረጽ ላይ ነን፡፡ በቅርቡ እነሱን ይዘን ከሕዝቡ፣ ከኢዜማ አባላትና ደጋፊዎች ጋር ውይይት ማድረግ ጀምረናል፡፡

*አሁን ካለው የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ብዛት ያለው ፖሊሲ መቅረጽ አስፈላጊነቱ ምን ድረስ ነው?*

መጀመሪያ ነባራዊ ሁኔታውን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ በሀገራችን ከመጋቢት 2010 ዓ.ም ከመጣው ለውጥ ጀምሮ ተከትለው የመጡ ግጭቶችና መፈናቀሎች አሉ፡፡ የኢትዮጵያ ችግር ህልቆ መሳፍርት የሌለው ነው፡፡ በእያንዳንዱ የሙያ ዘርፍና ሴክተር የኢትዮጵያውያን ችግር የትየሌሌ ነው፡፡ ለነዚህ ችግር መፍትሔ ማምጣት ያለብን በፖሊሲ የሃሳብ ልዕልና ነው ብለን እናምናለን፡፡ ለእያንዳንዱ ችግር ከአንድ በላይ መፍትሔ የምናመጣ ከሆነ ፖሊሲዎቻችን እየሰፉ ይሄዳሉ፡፡

*ኢዜማ በሚያዘጋጀው ፖሊሲ ምንድን ነው ማሳካት የሚፈልገው?*

ኢዜማ እንዲሳኩ ያስቀመጣቸው የማኅበራዊ ፍትህ እና የፖለቲካዊ ዘርፎችን ወደ ግብ ማድረስ የመጀመሪያው ነገር ነው፡፡ በቀጣይ ደግሞ ወደ ምርጫ እንገባለን፡፡ የፖሊሲ አማራጮቻችን ለሕብረተሰባችን አቅርበን፣ ሕዝብ ፖሊሲዎቻችን ላይ በቂ እውቀት ኖሮት እንዲመርጠን ነው እየሰራን የምንገኘው፡፡ ፖሊሲዎቹ በምሁራን እንዲሁም ከፍተኛ ልምድ ባካበቱ ባለሙያዎች የሚቀረጹ በመሆናቸው፣ የተረጋጋ የማይክሮ ኢኮኖሚ ኢትዮጵያ ውስጥ በመፍጠር ሕብረተሰባችን ከድህነት የሚወጣበት መንገድ ያመላክታሉ ብለን እናምናለን፡፡ የኢዜማ ፖሊሲ አላማ በቀጣዩ ምርጫ ሕዝቡ የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገውንም በመስጠት ሕብረተሰቡ ከድኅነት የሚያወጣበትን መንገድ ማስቀመጥ ነው፡፡

*ከአርባ በላይ ፖሊሲዎች እያዘጋጃችሁ መሆኑ በተደጋጋሚ ሲገለጽ ተሰምቷል፡፡ እያዘጋጃችሁት ያለው ፖሊሲ አልበዛም?*

ያሉን ፖሊሲዎች አንሰዋል ወይስ በዝተዋል? ማለት የምንችለው ከችግሮቻችን ተነስተን ነው፡፡ በፖሊሲ ሳይንስ እምነት ፖሊሲ ለመቅረጽ ስድስት አካባቢ ሂደት አለ፡፡ የመጀመሪያ አጀንዳ ማደራጀት የሚባለው ነው፡፡ ቀጥሎ ‹‹ችግሩ ምንድን ነው?›› ብሎ በጥልቀት ማወቅና መተንተን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የኢኮኖሚ/የማኅበራዊ ችግር ብናነሳ ኢትዮጵያውያን ከ80 በመቶ በላይ በጥልቅ ድህነት ውስጥ ነው ያሉት፡፡ ቁጥሩ ወደ 22 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ደግሞ በዓለም አቀፍ መረጃ መሠረት ፍጹም ድህነት ውስጥ ነው የሚኖረው፡፡ በዚህ መሠረት ይሄ የሕብረተሰብ ክፍል ከድህነት የሚወጣበትን መንገድ ማመቻቸት አለብን፤ የሚለው የፖሊሲ ሃሳብ እየሆነ ይቀጥላል፡፡ ከዛ ‹‹ምን መፍትሔ አለ?›› የሚለውን እንዘረዝራለን፡፡ ፖሊሲውን ለውይይት እናቀርባለን፡፡ በራሳችን ባለሙያዎች እንዲፈተሽ እናደርጋለን፡፡ ከዚህ ቀደም እንዳደረግነው ለምርጫ አስተባባሪ ካውንስል ለሌሎችም ሊሰሩ ይችላሉ ለምንላቸው የፓርቲው አባሎችና ደጋፊዎች እናቀርባለን፡፡ ከዛ በኋላ ነው ‹‹ፖሊሲ አለን›› ብለን ማውራት የምንችለው፡፡ ከችግሮቻችን ከተነሳን ▶

▶ ብዙ ችግሮች ስላሉብን ብዙ ፖሊሲዎች ይኖረናል፡፡ እንደውም ለወደፊት ፖሊሲዎቹ ቁጥራቸው በጣም ሊጨምር ይችላል፡፡

የካበተ የዴሞክራሲ ልምድ ያላቸው ሀገራት ፖሊሲዎቻቸውን በቁጥር እንኳን አያስቀምጡም፡፡ እኛ በቁጥር ያስቀመጥነው አሁን መሥራት ስለጀመርን ነው፡፡ የዛሬ አመት ገደማ 16 ብለን ነበር፡፡ ከዛ ውስጥ አንዱ ማክሮ ኢኮኖሚክስ የሚባለው ነው፡፡ ማክሮ ኢኮኖሚክስ ጥቅል ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የኢንደስትሪ፣ የገንዘብ በኋላ ደግሞ የሠራተኛ፣ የግብርና እና የሥራ እድል ፈጠራ ኢንተርፕርነር ፖሊሲዎች ከማክሮ ኢኮኖሚክስ ሃሳብ እየወሰዱ በግላቸው ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ ከዚህ በኃላ ቁጥሩ ሊጨምር ይችላል፡፡ የሕብረተሰባችንን ችግር መቅረፍ ከሆነ አላማችን ከ45 በላይ ነው፡፡ ለሕብረተሰቡ ከዚህም በላይ ይዘን መቅረባችን አይቀርም፡፡

*የምታዘጋጁቸው ፖሊሲዎች በየጊዜው የመሻሻል እድል አላቸው? ሊሻሻሉ የሚችሉባቸው ምክንያቶች ካሉ ቢጠቅሱልኝ?*

የፖሊሲ ሳይንስ ምሁራን ‹‹ፖሊሲ የመቅረጽ ሂደት የማያልቅ ነው›› ይላሉ፡፡ ፖሊሲ በየጊዜው ይሻሻላል፤ ይለወጣል፤ ይዳብራል፡፡ ኢዜማ የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች ዝግጅታቸው የተጠናቀቁትም ቢሆን በየጊዜው የሚፈተሹ ነው የሚሆኑት፡፡ በመሠረታዊነት ግን የኢዜማ ፖሊሲ ብለን አውጥተን የምናሳውቀው የኢዜማ ጉባኤ ሲያጸድቀው ነው፡፡

እስከዛ ባለው ሂደት የንግድ ፖሊሲ ላይ የሚሳተፉ ወደ ሰባት የሚሆኑ ምሁራን አሉ፡፡ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች በዚህ የንግድ ፖሊሲው ላይ እየተሳተፉ ነው፡፡ እነሱ ቀርጸው ሲጨርሱ በመጀመሪያ እነሱ ለቋሚ የጥናትና ምርምር ኮሚቴ ያቀርባሉ፡፡ እኛ ደግሞ አንዳንድ መሻሻል አለባቸው ብለን የምናስባቸው ነገሮች እንሰጣቸዋለን፡፡ ከዛም ከሀገር ውጭ ላሉ በዩኒቨርሰቲ ለሚያስተምሩ አባላትና ደጋፊዎች እንልክላቸውና እነሱ ሪቪው ያደርጋሉ፡፡ ከዛ ነው ለብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ እና ለኢዜማ ለምርጫ አስተባባሪ ማኔጅመንት ካውንስል የሚቀርበው፡፡

የመሻሻል ሂደቱ ሁልጊዜም የሚቀጥል ነው የሚሆነው፡፡ ለምሳሌ የገንዘብ ፖሊሲያችን ከአራት ወራት በፊት ነበር የተጠናቀቀው፡፡ የገንዘብ ፖሊሲያችን በተጠናቀቀበት ወቅት የሚቋቋሙ ባንኮች ስድስት እንደነበሩ ነው መረጃ ነበረን፡፡ አሁን ባለን መረጃ ከ20 በላይ ባንኮች ለመቋቋም በሂደት ላይ አሉ፡፡ እነዚህ ባንኮች የገንዘብ አቅም ያመጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ለእኛም ፖሊሲያችንን ድጋሚ የማሻሻል እና የማዳበር እድል ይሰጠናል፡፡

*አብዛኛው የሀገራችን ሕዝብ የሚኖረው በክልል ሲሆን የሚተዳደረውም በግብርና ሥራ ነው፡፡ ኢዜማ በምን አይነት መልኩ ነው ፖሊሲውን ለሁሉም ሕብረተሰብ በቀላል ቋንቋና አገላለጽ ተደራሽ ለማድረግ ያሰበው?*

ኢዜማ እንደሚታወቀው በ435 ምርጫ ወረዳዎች የተደራጀ ነው፡፡ በገጠር የሚኖሩትን የምናገኛቸው በእያንዳንዱ ወረዳዎች ነው፡፡ ለሕዝቡ በጹሁፍ እና ሕዝባዊ መድረክ በማዘጋጀት ፖሊሲዎቻችን የምናሳውቅ ይሆናል፡፡ ወደ ምርጫም ስለምንገባ የምርጫ ማኒፌስቶ እናዘጋጃለን፡፡ በምርጫ ማኒፌስቶ ላይ እያንዳንዱን ፖሊሲ በአጭር መንገድ የምንገልጽበትና የፖሊሲውን አቅጣጫዎች ምጥን መግለጫዎችን በማስፈር ለሕብረተሰባችን እንዲደርሰው እናደርጋለን፡፡

*ፖሊሲዎቹ በስንት አይነት ቋንቋ ይዘጋጃሉ?*

መጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ እንዲዘጋጅ ነው ያደረግነው፡፡ ምሁራን እንግሊዘኛ ቋንቋ ስለሚቀናቸው በእንግሊዘኛ ያዘጋጁታል፡፡ እኛ ራሳችን ወደ አማርኛ ለመመለስ ጥረት አድርገናል፡፡ በመቀጠልም ለሕብረተሰቡ በሌሎች ሀገር በቀል ቋንቋዎች ተደራሽ እናደርጋለን፡፡

*የኢዜማ ፖሊሲዎች ከዜግነት ፖለቲካ እሳቤ አንጻር እንዴት ይገለጻሉ?*

ከስያሜው ብንነሳ ፓርቲያችን የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ ነው የሚሰኘው፡፡ ፖሊሲዎቻችን የዜግነትን አጀንዳና የማኅበራዊ ፍትህን የሚያሰርጹ ናቸው፡፡ የኢዜማ የፖሊሲና የጥናት ምርምር ኮሚቴና የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ የማኅበራዊ ፍትህን በዚህ ፖሊሲ እንዴት ማሳካት እንችላለን? ፖሊሲው ሁሉም ዜጋ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ይገልጻል ወይ? የሚለውን እንፈትሻለን፡፡ አስቀድመን የምንመለከተውም ዜጎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ወይ? ማኅበራዊ ፍትህን ያሰፍናል ወይ? የሚለውን ነጥብ ነው፡፡ ▶


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ህዳር 30 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

***በኢትዮጵያ ውስጥ ፖሊሲን የተንተራሰ የምርጫ ክርክርና ውድድር ማድረግ ይቻላል ብላችሁ ታስባላችሁ?***

ሕብረተሰባችን የሚፈልገውም፣ የሚያስፈልገውም ብለን የምናስበው የፖሊሲ ሃሳቦች አማራጭ ሆኖ ይቀርብለታል፡፡ ሕብረተሰቡ የሚፈልገውንና ይጠቅመኛል የሚለውን ይወስዳል፡፡ ግጭት የሚመስሉ ክርክሮችን ሳይሆን የሚያስፈልገው ሕብረተሰቡ ወደፊት ህይወቱን የሚለውጥበት አይነት የፖሊሲ ክርክር ነው የሚያስፈልገው ብለን እናምናለን፡፡ በዝግጅት፣ በአቀራረብ እና በአማራጭ ከሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች ልንለያይ እንችላለን፡፡ የምናስበው ሌሎች ፓርቲዎችም ተዘጋጅተው ይመጣሉ ብለን ነው፡፡

ምሳሌ ለማቅረብ ያህል፣ የጤና ሥርዓታችን የምናዘምነው እንዴት ነው? አንዲት እናት ያለጤና እክል መውለድ የምትችለው እንዴት ነው? የኤች አይቪ ኤድስን እንዴት ነው የምንቆጣጠረው? በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ ነው የምንከራከረው፡፡ በምርጫው ሌሎች ፓርቲዎችም የፖሊሲ ሰነዳቸውን አቅርበው የሚከራከሩበት ነው ብለን ነው የምናስበው፡፡ ለዚህም ነው ዝግጅት እያደረግን ያለነው፡፡

***በጌት ፋም ሆቴል ሰባት ፖሊሲዎችን ለውይይት አቅርባችኋል፡፡ ለምን ሰባት ፖሊሲዎች ብቻ ልታቀርቡ ቻላችሁ? ሰባቱን ብቻ በምን ምክንያት ቅድሚያ ልትሰጧቸው ቻላችሁስ?***

ሰባት የሆኑበት ዋነኛው ምክንያት ከንግድና ኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ ከማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የተወሰዱ ሰነዶች ስለቀረቡበት ነው፡፡ ዝግጅታችን ከ40 በላይ ሲባል ነበር፡፡ እነዚህ የፖሊሲ ሰነዶች በሂደት የሚቀርቡ ነው የሚሆነው፡፡ የሁለት ቀናት አውደ ጥናት ነው ያካሄድነው፡፡ የመጀመሪያ ቀን የሚከራከሩት ባለሙያዎች ነበሩ፡፡ በዚህ አካሄድ ሰባቱንም ላንገመግም እንችላለን ብለን ነበር፡፡ ግን በሁለቱ ቀናት ውይይት ገንቢ አስተያየቶችን የተቀበልንበት መድረክ ነበር፡፡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ስናቀርብ ከማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ሥር እየተቀዱ የተሰሩ ፖሊሲዎችን ከእሱ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ነው ሰባቱን መርጠን ያቀረብነው፡፡ ወደፊት ኢዜማ ይለይበታል ብለን የምናስበውን በፖለቲካ ዘርፍ ሥር ያሉ ፖሊሲዎቻችን የምናቀርብ ይሆናል፡፡

***በሁለቱ ቀናት ውይይት ያገኛችሁት ምንድን ነው?***

በአመዛኙ ገንቢ አስተያየት ነው የተሰጠን፡፡ ይሄ ማለት የምናሻሽላቸው ነገሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ የቀረቡት ከንግድ እና ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎች ናቸው፡፡ በሀገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ንግድና ኢንቨስትመንትን የማያበረታታ መሆኑ ይታወቃል፡ ብዙዎቹ ተነቃቅተዋል፡፡ ባለሙያዎች በፖሊሲ ቀረጻ ላይ አሳትፉን እያሉ ነው፡፡ እኛም ከአስተያየታቸው ተነስተን ለጥናትና ምርምር ኮሚቴና ለብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያልቀረቡ ፖሊሲዎች ላይ እንዲሳተፉ ለማመቻቸት ጥረት እናደርጋለን፡፡

***ፖሊሲ ስትሰሩ ያጋጠሟችሁ ዋና ዋና ችግሮች የምትሏቸው ምን ምን ናቸው?***

በዋነኝነት እንደ ተግዳሮት ማንሳት የምንችለው የኮሮና ቫይረስ መከሰትን ነው፡፡ በወቅቱ በቡድን ሆኖ ተሰባስቦ ውይይት ማድረግ ባለመቻሉ ፖሊሲውን የመሥራት ሥራ ለጊዜውም ቢሆን ተስተጓጉሎ ነበር፡፡ ነገር ግን በሂደት ከሀገር ውጭ ያሉትን በዙም ውይይት እዚህም ያሉትን በኢሜልና በተለያዩ መንገድ መረጃ እየተለዋወጡ እንዲሰሩ ለማድረግ ጥረት አድርገናል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ካለባቸው የሥራ ጫና አንጻር ረጅም ጊዜ የወሰደባቸውም ሰዎች አሉ፡፡
አንዳንድ መስኮች ላይ ያሉን የሙያተኞች ቁጥር አነስተኛ ነው፡፡ ይህም ሌላ እንደ ተግዳሮት ሊነሳ የሚችል ነጥብ ነው፡፡ በጥቂት ሰዎች ብቻ እየተሰሩ ያሉ ሰነዶች አሉ፡፡ ከዛ ውጭ ጥሩ ድጋፍ እያደረጉልን ያሉ ከውጭ ያሉ የኢዜማ አባላትና ደጋፊዎች ናቸው፡፡ 28 የሚሆኑ የፖሊሲ ሰነዶቻችን ሪቪው ላይ ደርሰዋል፡፡ ከዛ ውጭ ከፍተኛ ጫና የሆነብን ነገር የለም፡፡

አንዳንድ ሰዎች የኢዜማ ከፍተኛ አመራሮች በሁሉም ፖሊሲዎች ላይ የሚሳተፉ ነው የሚመስላቸው፡፡ ፖሊሲዎቻችን በባለሙያዎች ነው የተቀረፁት፡፡ ኢዜማ እንደ ባህል የወሰደው የኢዜማ ፖሊሲ ከፖለቲከኞች ይልቅ በባለሙያዎች እንዲቀረፅ ነው፡፡

***በዚህ የፖሊሲ ቀረጻ ላይ እነማን እየተሳተፉ ይገኛሉ? ኢዜማ በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች ላይ መሳተፍ የሚፈልግ በምን አይነት መንገድ መሳተፍ ይችላል?***

የኢዜማ አባል ያልሆኑ ስማቸው እንዲገለጽ የማይፈልጉ ባለሙያዎች በፖሊሲዎቻችን ላይ ተሳትፈዋል፡፡ ወደፊት አባል ሆነው ከእኛ ጋር እንደሚሰሩም እናምናለን፡፡ ቀደም ብዬ ለማስተላለፍ እንደሞከርኩት ኢዜማ በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች ላይ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች፣ በተለያየ የምርምር ተቋማት የሚሰሩ ሰዎች እስካሁን ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ኢዜማ እየቀረፃቸው በሚገኙ ፖሊሲዎች ላይ መሳተፍ ፈልጌ አልተሳተፍኩም የሚል አካል፣ ኢዜማ በሚገኝባቸው ምርጫ ወረዳዎች ወይም በኢዜማ ዋና ቢሮ በመምጣት በፖሊሲዎቹ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ይችላል፡፡

***በእኔ በኩል ጥያቄዎቼን አገባድጃለሁ፡፡ ውይይታችን ከማብቃቱ በፊት የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ እድሉን ልስጥዎት፡፡***

የፖሊሲ ሥራዎቻችንን ማቅረብ ጀምረናል፡፡ በቀጣይ ደግሞ አራት ተመሳሳይ አውደ ጥናቶችን እናቀርባለን፡፡ በእነዚህ አውደ ጥናቶች ላይ ገንቢ እና የሰላ ትችት መሰንዘር የሚፈልጉ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ለኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ለጥናትና ምርምር ኮሚቴ ሃሳባቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ በፖሊሲ ቀረጻ መሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግዴታ የኢዜማ አባል መሆን አይጠበቅበትም፡፡ በኢዜማ የፖሊሲ ዝግጅቶች ላይ ገንቢ ሚና መጫወት እፈልጋለሁ ለሚል ማንኛውም ዜጋ ኢዜማ በሩ ክፍት ነው፡፡

***ለቃለ ምልልሱ ፍቃደኛ ስለሆኑ በዜጎች መድረክ ስም አመሰግናለሁ፡፡***

እኔም ስለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ፡፡



## የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ፓርቲው ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በተመለከተ ለባለድርሻ አካላት አሠራሩን ግልፅ ማድረግ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ፓርቲው ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በተመለከተ ለባለድርሻ አካላት አሠራሩን ግልፅ ማድረግ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

ሁላችንም እንደምንገነዘበው ዘመኑ የመረጃ ነው፤ የመረጃ አውታሮች ደግሞ በበይነ መረብ፣ በህትመት እና በብሮድካስት እየተስፋፉ የመጡበት፣ ቀላል ከሆኑ አካባቢያዊ ጉዳይች አንስቶ ትልልቅ ሀገራዊ አጀንዳዎች የሚያንሸራሽሩበት ፣ በተደራሽነትም በጥቂቶች የሚደመጡ አልያም ሚሊዮኖች ጋር ተድራሽነት ያላቸው፣ በባለሀብት ባለቤትነት የሚተዳደሩ ወይም የመንግሥት የሆኑ፣ ለአንድ ብሔር ወይም የፖለቲካ አስተሳሰብ ያዘመሙ ወይም ነፃ የሆኑ፣ በዓይነት ብዙ ሚድያዎች በሀገራችን አሉ።

ኢዜማ ሕዝብ ጋር ተደራሽ ለመሆን፣ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት ለማክበር እንዲሁም ተጠያቂነት ለማስፈን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በሕዝብ ግንኙነት ስር የተግባቦት ክፍል (communication department) አቋቁሞ ሥራዎችን እየተገበረ ይገኛል። በዚህ ክፍል ከሚሠሩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች አንዱ የሚድያዎችን ቃለ መጠይቅ ጥያቄ መቀበል እና ተገቢውን ሰው ለቃለመጠይቁ ማዘጋጀት እና መመደብ ይገኝበታል።

በኢዜማ የሕዝብ ግንኙነት አሠራር መሰረት ሁሉም የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ሥርዓት ጠብቀው፣ ለክፍሉ ቀርበው አስፈላጊው መመዘኛ ከተደረገ በኋላ ምደባ ይካሄዳል። ባለድርሻ አካላት ሊያውቋቸው ከሚገባ መመዘኛዎች ውስጥ የሚከተሉትን ትኩረት ሊያደርጉባቸው ይገባል።

1. በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎች ኢዜማን በተመለከተ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት የተግባቦት (Communication) ክፍል በኩል ማለፍ አለበት።
2. የመገናኛ ብዙሃን ከኢዜማ እንቅስቃሴዎች፣ የፖለቲካ አመለካከት እና ወቅታዊ ሁኔታዎች አንጻር ለሚያቀርቡት የቃለ መጠይቅ ጥያቄ የኢዜማን ሀሳብ በአግባቡ ሊያስረዳ የሚችል ኃላፊ የመመደብ ሙሉ ኃላፊነት የሕዝብ ግንኙነት ስር የሚገኘው የተግባቦት (Communication) ክፍል ነው። የመገናኛ ብዙሃን መረጃ ወይንም አስተያየት የፈለጉበትን ጉዳይ አሳውቀው ጥያቄያቸውን የማቅረብ እና ተገቢውን ምላሽ የማግኘት ሙሉ መብት አላቸው። ነገር ግን ምላሽ የሚሰጡትን የኢዜማ ኃላፊዎች የመምረጥ እና የመመደብ ሙሉ መብት የፓርቲው ነው።
3. የኢዜማ አመራር የሆኑን ሰው በግል ጉዳይ ወይም የተሰማሩበት ሙያዊ ሁኔታን አስመልክቶ መጠየቅ ከፈለጉ የአመራሩ የግል ጉዳይ በመሆኑ ከኃላፊው ጋር በቀጥታ ግንኙነት በመፍጠር መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በዚህ መልኩ የሚደረጉ ግንኙነቶችን ተጠቅሞ ኢዜማን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ማንሳት አይቻልም። ኃላፊዎችም በዚህ መልኩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን አያስተናግዱም።
4. ለቃለመጠየቅ ጥያቄ የሚያቀርቡ መገናኛ ብዙሃን ጥያቄያቸውን በስልክ +251944107661፣ በኢሜል ethzema@gmail.com ወይም ጽሕፈት ቤት ድረስ በአካል በመገኘት ማቅረብ ይችላሉ። የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ቀረፃው ከሚካሄድበት አንድ ሳምንት ቀድመው ማስገባት ይኖርባቸዋል። ይህ አሠራር በወቅታዊ ጉዳይ ላይ ምልከታን ለማወቅ የሚደረጉ አጭር ቃለ መጠይቆችን አይመለከትም።
5. መገናኛ ብዙሃን ጥያቄ ያቀረቡበት ቃለ መጠይቁ የሚቀርብበትን ፕሮግራም ስም፣ ቀን እና ሰዓት ከጥያቄያቸው ጋር ማሳወቅ አለባቸው። በአስገዳጅ ሁኔታ ሳይተላለፍ ከቀረ የተቀየረውን ሰዓት ከላይ በተጠቀሱት አድራሻዎች ማሳወቅ አለባቸው።
6. የተግባቦት (Communication) ክፍል ከመገናኛ ብዙሃን የሚመጡለትን ጥያቄዎች ሲያስተናግድ የመገናኛ ብዙሃኑን ቀደም ያለ ሥራዎች ገምግሞ የመገናኛ ብዙሃኑ የቀረጻ እና የአቀራረብ ጥራት ደረጃን በመገምገም የሚሰጠው ምላሽ ይህን መሰረት ያደረገ ይሆናል።
7. ኢዜማን አስመልክቶ የተሳሰተ መረጃ የሰጡ ፣ መረጃው የተሳሰተ መሆኑ በሕዝብ ግንኙነት ክፍላችን ተገልፆላቸው ማስተባበያ ለማስተላለፍ ፈቃደኛ ያልሆኑ መገናኛ ብዙሃን ጉዳዩን እንደአግባብነቱ ወደሕግ መውሰዳችን እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ከመገናኛ ብዙሃኑ ጋር ያለንን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል።
8. የተግባቦት (Communication) ክፍሉ የሚድያ ጥያቄን የሚያስተናግድበት መንገድ ላይ ቅሬታ ያለው አካል በመጀመርያ ቅሬታውን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ጋር pr@ethzema.org ማቅረብ ይችላል። ቅሬታቸው ምላሽ ካላገኘ ለፓርቲው ሊቀመንበር chairperson@ethzema.org ማቅረብ ይችላል።

# ‹‹ፖሊሲዎቻችን የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳሉ››

## አማን ይኹን ረዳ፣ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ

ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም(የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሲዘጋጅባቸው የቆየባቸውን የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽንና ቴክኖሎጂ፣ የኢንደስትሪ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ማኅበራዊ ከለላ፣ የገንዘብና የበጀት ፖሊሲዎቹን ለፓርቲው ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና ጥሪ ለተደረገላቸው ባለሙያዎች ቅዳሜ ሕዳር 26 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ሕዳር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በጌት ፋም ሆቴል ለውይይት አቀረበ፡፡

በውይይቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ፣ በያዝነው ዓመት ይካሄዳል ተብሎ በሚጠበቀው ሀገር አቀፍ ምርጫ ፓርቲዎች በፖሊሲ ሰነድ ዙሪያ ክርክር የሚያካሄዱበት እንዲሆን፣ ኢዜማ በምርጫ እንደሚሳተፍ አንድ ባለድርሻ አካል የራሱን አስተዋፅኦ እንደሚጫወት ገልፀዋል፡፡ ፓርቲያቸው ጥሩ አማራጭ ፓርቲ ሆኖ እንደመጣ የገለፁት ሊቀመንበሩ፣ ፓርቲያቸው ተመራጭ ሊሆን የሚችልባቸውን ሶስት ምክንያቶች አስረድተዋል፡፡

የድርጅት ቁመናቸው አንደኛው ምክንያት መሆኑን የጠቀሱት ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ፣ ፓርቲያቸው በመላ ሀገሪቱ ከ450 በላይ ወረዳዎች ላይ መዋቅር መዘርጋቱን ጠቁመዋል፡፡ በውጪ ሀገርም ከ30 ከተሞች በላይ የድጋፍ ማኅበሮች ማቋቋም መቻላቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ፓርቲያቸው ተመራጭ ሊያደርገው የሚችለው ሁለተኛው ምክንያት ጥሩ እጩ ማቅረብ መቻል መሆኑን የገለፁት ሊቀመንበሩ፣ በየወረዳቸው በችሎታቸው የሚመረጡ እጩዎችን ማቅረብ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡ አካባቢያቸውንም ሆነ የአካባቢያቸውን ችግር የሚያውቁ፤ በሕዝብም ዘንድ አመኔታ ያላቸውና ብቃት ያላቸውን እጩዎች በመለየት ለሕዝብ የሚያቀርቡ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በሕዝብ ዘንድ ኢዜማ እምነት እንዲጣልበት የሚያደርገው ሶስተኛው ምክንያት ጥሩ የፖሊሲ ሰነዶች ማቅረብ መሆኑን ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል፡፡ በሚመጣው ምርጫም ክርክር መደረግ ያለበት በፖሊሲ ዙሪያ መሆኑን የሚገልፁት ሊቀመንበሩ ‹‹ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዴት እንደታሰሩና እንደተዋከቡ የሚገልፁበት፤ ገዢው ፓርቲም ጁንታውን እንዴት እንደደመሰሰ የሚገልፅበት ክርክር የሚካሄድ ከሆነ፤ ይሄ የምርጫ ክርክር አይደለም›› በማለት የምርጫ ክርክሩ በፖሊሲ ዙሪያ ሊሆን እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡ ፓርቲያቸው ለዚህም ብሎ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ 45 ያህል ፖሊሲዎችን ▶





መቅረፁን ጠቁመዋል፡፡

ከሊቀመንበሩ በመቀጠል የኢዜማ መሪ ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ‹‹የሀሳብ ፖለቲካ በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሀሳብ ፖለቲካ አስፈላጊነትን የዳሰሱበትን ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ ፖለቲካው ላለፉት 30 ዓመታት ተነክሮ ከቆየበት የዘር ፖለቲካ መውጣት እንዳለበት የጠቀሱት መሪው፣ የፖለቲካ ማኅበረሰቡን አባል በዜግነት ደረጃ ማየት የሚችል ፖለቲካ ውስጥ መግባት እንደሚያስፈልግ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡ ‹‹እስከዛሬ የነበረው ፖለቲካ፣ ፖለቲካ አልነበረም›› ሲሉ የተደመጡት መሪው ብርሀኑ ነጋ፣ የእስካሁኑን ፖለቲካም ‹‹የመናቆር ፖለቲካ ነው የነበረው›› ሲሉ ኮንነውታል፡፡ ‹‹ፖለቲካ ማለት የሀሳብ ግጭቶች ነው›› ያሉት መሪው ልዩነቶች በሰከነና ምክንያታዊ በሆነ አካሄድ የሚወሰኑበት ፖለቲካን መከወን እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመፍጠር እድል እንዳለ ያወሱት መሪው፣ መንገዱ ግን አልጋ በአልጋ እንደማይሆን ጠቁመዋል፡፡ ሲያጋብሱት በነበረው ጥቅም የተነሳ የዴሞክራሲያዊ ስርአት መዘርጋት ይጎዳናል ብለው የሚያስቡ ሀይሎች እንዳሉ የጠቀሱት ብርሀኑ ነጋ፣ እነዚህ ሀይሎች በቀላሉ ተሸንፈናል ብለው እንደማያስቡ ተናግረዋል፡፡ ይህንንም አውቆ መንቀሳቀስ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የብዙሁኑ ስርአት ነው ተብሎ ከታመነም አብዛኛውን ማኅበረሰብ ለዚህ ተገዢ እንዲሆን ለማድረግ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ በሀሳብ ላይና በምክንያት ላይ ለተመሰረተ ፖለቲካ ፓርቲያቸው እየተዘጋጀ መሆኑን የጠቀሱት መሪው፣ ‹‹ፖለቲካ የሀሳብ ትግል ነው፤ በሀሳብ ደረጃ በልጦ ለመገኘት መዘጋጀት አለብን ስንል በአጭር ጊዜ ይሆናል ማለት አይደለም›› በማለት ስክነትና ትእግስትም እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል፡፡

ከመሪው ብርሀኑ ነጋ በማስከተል የኢዜማ ምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ካውንስል የመንግሥትና የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ የሆኑት አማን ይኹን ረዳ፣ የፓርቲያቸውን የፖሊሲ ዝግጅት በማስመልከት ሰፋ ያለ ማብራሪያ አቅርበዋል ፡፡

የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው ድርጅታቸው ኢዜማ የሀገሪቷን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት ሂደት ላይ መሆኑን በመጥቀስ፣ ፓርቲያቸው ሀገሪቷ የምትገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ የተረዳ፣ ከወረዳ ጀምሮ ሕብረተሰቡ ችግሮቼ ናቸው የሚላቸውን አንገብጋቢ ችግሮች ትኩረት ሰጥቶ በመለየትና በማደራጀት ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረገ የፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ሲከተል እንደቆየ ገልፀዋል፡፡ በዚህ መሰረትም ከ40 በላይ ፖሊሲዎችን መቅረፅ መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በያዙት የፖለቲካ ፍልስፍና ብቻ ሳይሆን ችግሮችን ለመፍታት በሚያቀርቡት አማራጭ ሀሳብ ጭምር ብቻ ነው መምረጥ ያለባቸው ስንል እዛ አልደረስንም በሚል የሚሞግቱን አሉ›› ያሉት የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው፣ ኢዜማ ሀገሪቷ የምትገኝበትን ሁኔታ በውል ተረድቶ ሀገሪቷ ላይ የተደቀኑባትን ችግሮች መወጣት የሚቻለው ግልፅ የሆነ አማራጭ ፖሊሲ ማቅረብ እንደሚገባ በማመን መሆኑን ተረድቶ ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡ እየተቀረፁ ያሉት ፖሊሲዎቹ በማኅበራዊ፣ ፖለተካና ኢኮኖሚ ዘርፍ ተከፍለው መቀረፃቸውን አማን ይኹን ረዳ ጠቁመዋል፡፡

በማኅበራዊ ዘርፍ የተቀረፁት ከ15 በላይ ፖሊሲዎች ማኅበራዊ ፍትህን ከማስፈን አንፃር ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ሲሆን ኢትዮጵያውያን የእኩል እድል፣ የእኩል መብትና የእኩል አያያዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከድህነትና ከአለእኩልነት (Inequality) ተላቀው ከስጋት ነፃ ሆነው እንዲኖሩ ታሳቢ ተደርገው የተቀረፁ ፖሊሲዎች መሆናቸውን የፖሊሲ አስተባባሪው አስረድተዋል፡፡

በኢኮኖሚ ዘርፍ ከ20 በላይ ፖሊሲዎች መዘጋጀታቸውን የገለፁት የፖሊሲ አስተባባሪው፣ የሕብረተሰቡን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት የሚችል የኢኮኖሚ ስርአት መገንባት በኢኮኖሚው ሥር የተቀረፁ ፖሊሲዎች አብይ አላማ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የምግብ ዋስትናና ለመኖሪያ ቤት ፖሊሲ በእጅጉ ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩም ገልፀዋል፡፡

‹‹በዘላቂነት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ጥቅም ከማስከበር አንፃር ውጤታማ ሥራ ሰርተናል ማለት የምንችለው ኢኮኖሚው በመንግሥት ብርቱ ክንድ የሚዘወር ሳይሆን በሀገር በቀል ባለሀብቶች የሚንቀሳቀስ እንዲሆን ማድረግ የቻልን ሲሆን ነው›› ያሉት የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ፣ ፓርቲያቸው ለሀገር በቀል ባለሀብቶች ትኩረት ሰጥቶ ሀገር በቀል ባለሀብቶችን አቅም መገንባት ላይ እንደሚሰራና ለሀገር በቀል ባለሀብቶች የተሻለ እድል የሚፈጥሩ ሥራዎችን እንደሚያከናውን አስረድተዋል፡፡ ይህን ሲሉ ግን የውጪ ባለሀብቶችን አንፈልግም እያሉ እንዳልሆነ አስረድተዋል፡፡ በኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻቸው አማካኝነት ፈጣን፣ መሰረተ ሰፊና ድህነትን በቤተሰብ ደረጃ ከማሸነፍ አንፃር ትልቅ ጠቀሜታ ያለው የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን በሀገሪቱ ላይ ለማከናወን እንደሚፈልጉ የፖሊሲ አስተባባሪው ጠቁመዋል፡፡

በፖለቲካ ዘርፍም ኢዜማ 10 ፖሊሲዎችን መቅረፅ መቻሉን የጠቆሙት የፖሊሲ አስተባባሪው፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ከማስፋት፣ የዜጎችን የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤትነታቸውን ከማረጋገጥ፣ ሕገ መንግሥታዊ ስርአትና መንግሥታዊ ተጠያቂነት ከማስፈን፣ የፍርድ ቤቶች ነፃነት ከማስከበር እንዲሁም የሀገር ሰላምና የግዛት አንድነትን ከማስጠበቅ አንፃር በፖለቲካ ዘርፍ ሥር ያሉት 10 ፖሊሲዎች ትልቅ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

በሶስቱም ዘርፍ ሥር ያሉት ከ40 በላይ ፖሊሲዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤትነቱን ያረጋግጣሉ ብለው እንደሚያምኑ የፖሊሲ አስተባባሪው አማን ይኹን ረዳ ተናግረዋል፡፡ ቅዳሜ ሕዳር 26 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ሕዳር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በጌት ፋም ሆቴል በተካሄደው የፖሊሲ አውደ ጥናት ላይ ለውይይት የቀረቡት የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽንና ቴክኖሎጂ፣ የኢንደስትሪ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ማኅበራዊ ከለላ፣ የገንዘብና የበጀት ፖሊሲዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ፖሊሲዎች ለውይይት የሚቀርቡበት 4 አውደ ጥናቶች በቀጣይ ወራት እንደሚዘጋጁ ዜጎች መድረክ ለመረዳት ችላለች፡፡

# ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ፆታዊ ጥቃት በተመለከተ የፓናል ውይይት የሚካሄድ ይሆናል

**ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም(የዜጎች መድረክ)**

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የሴቶች ጥቃት በሚመለከት ግንዛቤ የሚያስጨብጥ የፓናል ውይይት ቅዳሜ ታህሳስ 03 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ታህሳስ 04 ቀን 2013 የሚያካሄድ መሆኑን የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ትእግስት ወርቅነህ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

የፓናል ውይይቱ አብይ አላማ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን የፆታ ጥቃት በተመለከተ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና በአዲስ አበባ የሚገኙ የኢዜማ አመራሮችና አባላት ችግሩን ለመከላከል የሚያስችል አቅም ላይ እንዲደርሱ ስልቶችን መቀየስ መሆኑን ተጠሪዋ አስረድተዋል፡፡ ውይይቱ ቅዳሜ ታህሳስ 04 ቀን 2013 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በአራት የተለያዩ አካባቢዎች በ8 ሰአት የሚደረግ ሲሆን፤እሁድ ታህሳስ 05 ቀን 2013 ዓ.ም ቀጥሎ በ8 ሰአት በኢዜማ ዋና ፅህፈት ቤት በመስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ይሆናል፡፡

የፓናል ውይይቶቹን የኢዜማ ሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣ ከሌሎች የድርጅቱ አመራሮችና በስነፆታ ላይ ከሚሰሩ አካላት ጋር የሚመሩት ይሆናል፡፡

# 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ የተሳካ እንዲሆን ሁሉም ወገን የሚቻለውን ጥረት እንዲያደርግ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ባለም አቀፍ ካውንስል ጥሪውን አቀረበ

**ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም(የዜጎች መድረክ)**

ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ዓለም አቀፍ ካውንስል «አሻራ ለዴሞክራሲ» በሚል መሪ ቃል ሰፋፊ ሥራዎችን ለመስራት እንቅስቃሴ መጀመሩን አስታወቀ፡፡

ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ዓለም አቀፍ ካውንስል የተቋቋመው የዜግነት ፖለቲካና ማኅበራዊ ፍትህ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰፍን የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ሲሆን፣ ከኢዜማም ጋር በቅርበት የሚሰራ ነው፡፡ የካውንስሉ የዘመቻ አላማ ኢትዮጵያዊያን በዘላቂ መፍትሄዎች ላይ እንዲያተኩሩ በቀጣይነት ማስገንዘብና በአገራቸው የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ በጎ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ የማስተባበር ስራ መስራት መሆኑን ካውንስሉ ገልጿል፡፡ ካውንስሉ፣ ኢዜማ በተቋምነት የተደራጀ ጠንካራ ፓርቲ እንዲሆን የሚችለውን እገዛ ሁሉ የሚያደርግ መሆኑን የገለፀ ሲሆን፤ ከምርጫ 2013 ጋር ተያይዞ ኢዜማ ለሕዝቡ አማራጭ ሀሳቦችን የሚያቀርብ ብርቱ ተፎካካሪ እንዲሆንና በዲሞክራሲ ባህል ግንባታው ላይ ጉልህ ሚና እንዲጫዎት የተቻለውን የገንዘብ፣ የእውቀት፣ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ አስቀድሞም ይሁን ሰሞኑን የሚስተዋለው ችግር የሚመነጨው ከፖለቲካዊ ባህልና ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ተተክሎ ከቆየው የዘውግ ፖለቲካ መሆኑን ያወሳው ካውንስሉ፣ ለዚህ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት የዘውግ ፖለቲካን ወደ ሀሳብ ፖለቲካ መቀየርና የፖለቲካ ስርአቱን ዲሞክራሲያዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል፡፡ በየዕለቱ የሚከሰቱት ፖለቲካዊ ችግሮች ትኩረት የሚስቡ ጉዳዮች ቢሆኑም፣ ኢትዮጵያዊያን ከነዚህ እለታዊ ክስተቶች ባሻገር ባሉ ዘላቂ መፍትሄዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉና በእጃቸው ውስጥ የገባው የለውጥ እድል ፍሬያማ እንዲሆን የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ካውንስሉ ጥሪውን አቅርቧል፡፡

በ2013 ዓ.ም. ምርጫ እንደሚደረግ በመንግሥት በኩል እየተነገር መሆኑን የጠቀሰው ካውንስሉ፣ ይህን ምርጫ ለማድረግ የሚያስችሉ መደላድሎች አቅም በፈቀደ መጠን ከተመቻቹና ምርጫው ነፃ፣ ፍትሃዊና ተአማኒ የሚሆን ከሆነ፣ የሀገሪቷ የፖለቲካ ስልጣን በሕዝብ ድምፅ ወደሚወሰንበት ዲሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ እንዲገባ ሰፊ እድል ይፈጥራል ብሎ እንደሚያምን በመግለፅ የ6ኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ታሪካዊነትና ያለውን ትልቅ ጥቅም ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ምርጫው የተሳካ እንዲሆን ሁሉም ወገን የሚቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ ካውንስሉ ጥሪውን አስተላልፏል፡፡

የ2013 ምርጫ ጠንካራ ፉክክር የሚታይበት ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መሆን ይገባዋል የሚሉና የዜግነት ፖሊቲካና ማኅበራዊ ፍትህ በሕዝቡ ዘንድ ተመራጭ እንዲሆን ጽኑ ፍላጎት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከካውንስሉ ጎን በመሰለፍ የድርሻቸውን እንዲወጡና የትውልድ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ ካውንስሉ ጥሪውን አቅርቧል፡፡





# የምርጫ ወረዳዎች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጡ የሚያደርግ ስልጠና ተሰጠ

**ህዳር 30 ቀን 2013 ዓ.ም(የዜጎች መድረክ)**






የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ባሳለፍነው እሁድ ሕዳር 27 ቀን 2013 ዓ.ም በመስፍን ወልደማሪያም አዳራሽ በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ ለተለያዩ የምርጫ ወረዳዎች ስልጠና ሰጠ፡፡

የስልጠናው አብይ አላማ ኢዜማ በ2013 ምርጫ በዋንኛነት የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ በሚያደርግበት የምርጫ ወረዳዎች የሚገኙ የአመራር አባላት፣ በምርጫ ወረዳዎቹ ለማድረግ የታሰቡትን ዝግጅቶችና ዘመቻ ተረድተው፣ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጡ ማድረግ መሆኑን ኮሚቴው ለዜጎች መድረክ ገልጿል፡፡

ስልጠናውን ካገኙት የአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳዎች መሀል ምርጫ ወረዳ 2 እና 14፣ 3፣4፣5፣6 እና ምርጫ ወረዳ 7 ይገኙበታል፡፡

ስልጠናው ቀጣይነት ያለው ሲሆን ምርጫ ወረዳ 8፣ 1 እና 9፣ 10፣11፣ 12 እና 13፣ 15፣16፣17፣18፣19፣20፣21 እና 22፣ 23፣24፣25፣ 26 እና 27 ስልጠናውን የፊታችን ቅዳሜ ታህሳስ 3 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ታህሳስ 4 ቀን 2013 ዓ.ም ስልጠናውን የሚያገኙ መሆናቸውን ከምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡

የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ከአዲስ አበባ ከተማ በተጨማሪ በተለያዩ ክልል ከተሞችም ለምርጫ ዝግጅት የሚረዱ የተለያዩ ስልጠናዎችን ሲሰጥ እንደቆየ የሚታወቅ ነው፡፡